# የየካቲት 66 ምላሽ ያጡ ጥያቄዎች

ለዘመናት ኢትዮጵያን ሲያስጨንቅ ሲያደማ የቆየውን የኋላ ቀር ስርዓት ነቅሎ ለመጣል፤ ለማስወገድና ስር ነቀል ለውጥ ሊያመጣ የመጣው የየካቲት 66 አብዮት ጥያቄዎቼ በሚል ያነሳቸው መሰረታዊ ጉዳዮች/ መፈክሮች ቢሟሉ ኖሮ ሀገራችን ኢትዮጵያ እውነትም የብልጽግናና የዴሞክራሲ ጮራ ሆና በመላ አፍሪካ በፈነጠቀችና ታሪኳን አድሳ በተገኘች ነበር።

የየካቲት 66 መሰረታዊ መፈክሮች መሬት ለአራሹ፤ ዴሞክራሲ ለጭቁኑ ሕዝብ፤ እኩልነትና ሉአላዊንት የሚሉ ነበሩ። በፖለቲካውም ሆነ በማህበረሰብና ኤኮኖሚያዊው መስክ የተነሱት የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ብዙሃኑን ሊያነሳሱና ሊያስተባብሩ ችለዋል። እኩልነት በብሄረስብም ሆነ በሀይማኖት መስክ ተጠይቆ ነበር። አብዮቱ ግን በመኮንኖች መፈንቅል ተድናቅፎ ደርግ የሚባል አረመኔ ለስልጣን ሲበቃ የሕዝቡን ጥያቄ ከትቢያ ጣለው። መሬት ለአራሹ መሆኑ ቀርቶ ለወታደራዊው አገዛዝ ሆነ። የአርሶ አደሩ ጢሰኝነትም ቀጥሎ የሚገብረው ለዚሁ ራሱን መንግስት ላለው ሀይል ሆነ። ዴሞክራሲ በመኮንኖች አምባገነንነት ተተካ--ሕዝብ ሞግዚት ያስፈልገዋል ተብሎ ተወሰነበት። ይህን የታገሉትም የተሰጣቸው መልስ ነጻ እርምጃና ቀይ ሽብርም ሆነ። እኩልነት ተሰረዘ። ለውጥ መጣ ግን ከለውጡ በፊት የነበረው ሁኔታ ከፍቶ ቀጥለ። የዚሁ አዲስ አገዛዝ ደጋፊዎችም አስፍስፈው ተነጠፉ። እምቢኝ ያሉ ተረገጡ፤ ተጨፈጨፉ። ለየካቲት አብዮት ምክንያት የሆኑት በደሎች በመቀጠላቸው ወታደራዊ አገዛዝ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሲተካም ያው የገማው የገለማው ሁኔታ--ያውም ተባብሶ--ቀጠለ፤ እስካሁንም አለ። ኢትዮጵያም ሰላምና ዴሞክራሲን አጥታ በስቃይ ላይ አለች።

ለዚህም ነው የአብዮቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ አጥተው ቀጠሉ--ችግሩም ተባባሰ የምንለው። የሀገራችን አብዛኛው ህዝብ በገጠር የሚኖርና ቤእርሻ የሚተዳደር ነው። ብዙሃኑ ስንልም ይህንኑ ይመለከታል። ብዙሃኑ አርሶ አደር ደግሞ የመሬቱና የምርቱ ባለቤት መሆንን ይፈልጋል። አትፈልግም የሚሉት ክፍሎች አማክረውትም ወይም ጠይቀውትም አያውቁ። በእናውቅልሀለን ግን ተመጻድቀው ራሳቸውን የአርሶ አደሩ የበላይ ጠባቂና ወሳኝ ይሆናሉ። ወያኔም የቀጠለው ከሞላ ጎደል የኮታ መንግስት ይባል የነበረውን የደርጉን ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግስት እንዳይቋቋም መሰሎቹና ተለጣፊዎችን ይዞ የራሱን ከፋፋይና ዘረኛ አገዛዝ መሰረተ፡፡ ቀደም ሲል ደርጉም ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይመስረት ሲባል በአውናባጅ መፍክሮችና አቋሞች ተመስርቶ አሻፈረኝ በማለት የራሱን ጭፍን አምባገነናዊ አገዛዝ መስርቶና በአድርባይ ምሁራን ተደግፎ ሕዝብን ቀጥቅጦ ለ17 መራራ ዓመታት ገዛ። በመጨረሻም መሪያቸው ነኝ ያለው አረመኔ ኮልኔል ሀገር ዘርፎና ፈርጥጦ ሐራሬ ዚምባብዌ

ገባ። ነፍሰ ገዳዩንም ነፍስ ሊዘሩለትና ታሪኩን ሊያድሱለትም የሚጥሩ ጉዶችም ዛሬ መፍላታቸውን መታዘብ ተገደናል። መሬት ለአራሹ የዴሞክራሲና የሙብትም ጥያቀ ሆኖ ምላሽ በማጣቱ ከፖለቲካ ቀውስ የመውጣት ዕድል ክርችም ብሎ ተዘግቶ ቆይቷል ማለት የሚቻል ነው። በዘመነ ወያኔ ደግሞ የእኩልነት ጉዳይ አፈር በልቷል ማለት ይቻላል። በሀይማኖት ጉዳይ አገዛዙ ጣልቃ እየገባ ተቃውሞ ቀጥሎበታል። ምርጥ ዜጋ ፤ ወርቅ ዜጋ ክልል አንድ የሚባልም መጥቶ ቀሪው ሕዝብ በሁለተኛ ደረጃ ዜጋነት በመረገጥና፤ በመመንጠርና በመፈናቀልም አለ። ዘረኝነት መረን ለቆ ሚሊዮኖችን እያደማ እያስለቀሰም ነው ። ወያኔ ደርግ ያፈነውን የካቲት ጥልቅ ጉድጓድ ቆፍሮ እየቀበረው ነው።

ዴሞክራሲ ለጭቁኖች አለገደብ ብሎ መጠየቅ ደግሞ በደርግ ጊዘ ሞትና ሽብር እንደዳረገው ሁሉ በወያኔም የሚያስጠቃ መፈክሮ ሆኗል። ወያኔና ዴሞክራሲ ተጻራሪ ናቸውና ነጻ ጋዜጠኞች፤ ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ ሰላማዊ ሰልፈኞች፤ ድምጻችን ተሰረቀ ባዮች፤ ሙብትና እኩልነት ጠያቂዎች ሁሉ ጸረ ሰላም ጸረ አብዮት ተብለው ታፍነዋል፤ ተገድለዋል፤ ተግዘዋል፤ ስየል ተቀብለዋል፤ ደብዛቸው ጠፍቷል። አድር ባይ ምሁራን ወታደራዊውን አገዛዝና አረመኔውን ኮለኔል ደግፈው እንደነበረው ሁሉ የወያኔ ተለጣፊዎችና የወንጀል ተባባሪዎችም ይህንን ሀገር አጥፊ ቡድን እየደገፉና የሕዝብ ጠላት ሲሞትም ደረት እየመቱ እያለቀሱም ሸኝተዋል። ወያኔም በራሱ ላይ የሚመጣበትን አይቀሬ አብዮት ጊዜ ለማራቅ በሆድም በሀይልም እየገዛ በስልጣን ከደርግ በላይ ጊዜ እነሆ ቆይቷል። የሕዝብ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ አጥተው የህዝብ አፋኝ ሀይል በባዕዳን ድጋፍ በሀገሪቷ ላይ ተጭኖ ባለበት ለለውጥ አምጪ አመጽ የሚያስፈልገው ቆራጥ ትግልና ትብብር ግን ደብዝዞ በመገኘቱ የወያነ እድሜ ሊራዘም ችሏል። ለወያኔ ጊዜ ይስጠው፤ ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል (የሰለቸውስ መበደልና መጨቆን ነበር!)፤ ትጥቅ ትግል አያዋጣም፤ አሜሪካንን መማጸናችን ይጠንክር፤ ወያኔ ከወደቀ ሀገር ትጠፋለች፤ ጨዋ ሰላማዊ ማድረጉ ይበቃናል፡ ወዘተ እያሉ፤ ጸረ ወያኔ ቁርጠኛ ያገር ልጆች ላይ እየዘመቱ ለወያኔ ድልዳል መሬት ያዘጋጁም ላለው ሁኔታና ለሀገራችን መጎዳት ተጠያቂ ናቸው። ወጣም ወረደም ግን ሀገራችን ህልውናዋን ጠብቃና መሰረታዊ የህዝብ ጥያቄዎችም ተመልሰው አንድነቷ የተጠበቀ ዴሞክራሲያው ሀገ ትሆን ዘንድ ወያኔን ከነግሳንግሱ ጠርጎ ወደ ጉድጓድ መጣል ያስፈልጋል። ይህን ብሔራዊ ግድጅ የዘነጋ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነኝ ብሎ ቢናገር ሀሰት ይሆናል። ያለፉት 22 ዓመታት ደግሞ የለውጡ መንገድ ምን መሆን እንዳለበት ቁልጭ አድርገው አሳይተውናል። ከአመጽና ትጥቅ ትግል ውጪ መፍትሔ የለም። ወያኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጸረ ኢትዮጵያዊነቱ ይብሰበታል እንጂ ሲቀንስ አልታየም -- በመሆኑም ከወያኔ ጋር እርቅ የሚስብኩ ሁሉ ቅዠታሞች ወይም የወያኔ ጀሌዎች ቢባሉ ስህተት አይደለም። ሰላማዊ ትግልን ከአመጽና መሰል ትግሎች ለይተውና አቃርነው የሚያዩትም ራሳቸውንና ህዝብንም ማታለላቸው በገሃድ ታይቷል። ማመጽ የህዝብ ሙብት ነው--ጭቆና ባለበት ደግሞ አመጽ የህዝብ ግዴታ ነው። ይህን መካድ ደግሞ ራስን ለባርነትና ለጭቆና ሰለባ ማድረግ

ነው። ኢትዮጵያ ሞት አይፈሬ ጀግኖችን ስታፈራ የቆየች ነበረችና አለጊዜው መከነች ልንል ባይዳዳንም ይመረጣል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የደም ግብር ከፍሎ ለሙብቱና ለሀገሩ መታገሉን የየካቲት አብዮትና ከዚያም ተከትሎ የተከሰተው ሁኔታ ሁሉ ምስክር ሆኖለታል። በጸረ ወያኔ ትግልም ብዙዎች መስዋዕት ሆነዋል። ይህ ቆራጥና የትግል መንፈስ ይጠናከር ዘንድ ወያኔን በሁሉም መስክ መቋቋም የግድ ነው። መከፋፈልን ማስወገድና ክንድን ማስተባበር ያስፈልጋል። ይህ እውን ይሆን ዘንድ በህዝብ ጎራ ውስጥ ሆነው ክፍፍልን የሚያነግሱትን ማጋለጥና ከጥቅም ውጪ ማድረግ ወሳኝ ነው። የሕዝብ ጎራ ከጾዳም በኋላ ምላሽ ጠያቂው ሌላ አቢይ ጉዳይ ትግሉስ እንዴት የሚለው መሆን አለበት። ጠላት በሃያላን እየተደገፈ ነውና ይህንን ርባና ቢስ ለማድረግ ስልት መቀየስ አስፈላጊ ነው። ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ሀይሎችና ሀገሮች ጋ ሄዶ መወሸቅ ወይም እርዳታን መፈለግ ራስን ጠልፎ መጣል ነው--ለውድቀት የወያኔም ጥረትን የማይጠይቅ ማለት ነው። ስለዚህ ጠላትን ማወቅ እንደሚገባው ሁሉ ማነው ወዳጅ የሚለውንም ጠንቅቆ ማወቅ ያሻል። በዚህ መስክ የታየው ድክመት ለሕዝባዊው ትግል መዛል ከባድ አስተዋጾ ማድረጉ ሊካድ የሚችል አይደለም። ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

1ኛ/ ሰፍኖ ያለውን ለቀተኝነት አስወግዶ የሕዝብን ጎራ ከአስመሳዮች፤ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች፤ ከወያኔ ቅጥረኞች፤ ከባዕድ ቡችሎች ማጽዳት፤

2ኛ/ በኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ ላይ ምንም አለማወላወል፤ ትምክህትንም ሆነ ገንጣይነትን መዋጋት፤

3ኛ/ የአንድነት ሀይሎችን ህብረት እውን ለማድረግ መረባረብ፤

4ኛ/ ወያኔ የሕዝብና የሀር ጠላት ነውና በዚህ ላይ ምንም ብዥታ ሳይኖር በጋራ ለውድቀቱ መታገል ፤

5ኛ/ የሕዝብን ጎራ ከሰርጎገቦችና አፍራሾች ጥቃት መከላከል።

ከየካቲት 66 አብዮት ተመክሮ ብዙ መማር እንችላለን። አብዮቱ መጨርሻ ድሉን ባያገኝም አሮጌውን ስርዓት በማስወገድ ድልን አስመዝግቧል። የመሪ ድርጅት ወሳኝ ሚናንም ያሰምርበታል። ለድል ደግሞ መስዋዕትነት አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራል። ዛሬ ታግሎ የተሰዋ ሁሉ ተፈጀ ተሞኘ የሚሉትን ስህተታቸውን ይጠቁማቸዋል። ትግልና ድል አልመስዋዕትነት ከቶም ሆነ መቼም የሚገኝ አይደለም -- ለዚህም ነው መስዋዕትነት አልባ ድልን የሚሰብኩ ወደዱም ጠሉም ለወያኔ የሚጠቅም ሚና ይዘው ያሉት። በወያኔ አጋፋሪነት በኢሕአፓ ላይ የተከፈተው ታሪክ በራዥ ዘምቻ (መጽሃፍት ወዘተ) ግቡ ሕዝብ ና ትውልድ ከመረረ ትግል እንዲርቅ ለማድረግ ለማስፈራራት ነው። ትከሻችሁ ለጠመንጃ ሳይሆን ለአዛባ ሸክም ቢውል ይሻላል ለማለት።

በሰሞኑ አንድ ኢትዮጵያዊ አይሮጵላን ጠልፎ ወያኔን ሲያጋልጥ ለምን ጠለፈ ብለው ሊያወግዙት የተነሱት ምንኛ የወያኔ ቆሻሻ ተሸከሙ ቅስቀሳ እንደሰራ ጠቋሚ ነው፡፡ መጥለፍ አንድ ከዚያና ከእዚህ በላይ ደግሞ እርምጃ ይሁን ይብዛ የሚባል ነው እንጂ ቅንጣትም የሚተች አይደለም። ይህን መረዳት ያስፈልጋል። ጸረ ወያኔው ትግል መስዋዕትነትን ይጠይቃል። የተገደሉት እና በወያኔ ህይወታቸው የጠፉ ጀግኖችን እናከብራለን፤ አርአያ እናደርጋቸዋለን እንጂ፤ በቃሊቲና በዝዋይ ወዘተ እየማቀቁ ያሉትን ዜጎች አይዞን ጎናችሁ ነን እንላለን እንጂ አጠፉ የምንል ሊሆን አይገባም። የጸረ ግራዚያኒ አርበኞችን፤ የየየካቲት 66 ጀግኖችን፤ ጸረ ወያኔ ሰማዕትን ሁሉ እናደንቃለን እንጂ ታግለው የሞቱትንና ወይም ያታገላቸውን ድርጅት በማውገዝ በራሳችን ሰብዕና ላይ ግድያ አንፈጽምም፡፡ ጠለፉ ፤ ጥቃት በየፈርጁ ወያኔ ላይ መድረስ አለበት--ይህ ቅር የሚላቸው ካሉ ወያኔ መሆናቸውን በተጨባጭ ማመን ይገደዳሉ ወይም የሕዝብ ትግል ይነግራቸዋል። እማዬ ሀግሬ ማለት እማዬ ምንሽርን ታጥቆ ነው የተባለው መረሳት የለበትም።

ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም!